**Español:** masspowerchoice.com/cambridge/letter_spanish.pdf
**Kreyòl ayisyen:** masspowerchoice.com/cambridge/letter_hcreole.pdf
**বাংলা:** masspowerchoice.com/cambridge/letter_bangla.pdf
**አማርኛ:** masspowerchoice.com/cambridge/letter_amharic.pdf
masspowerchoice.com/cambridge/letter_arabic.pdf **:عربي**

# የካምብሪጅ ከተማ

## የማሕበረሰብ የሙብራት/ኤሌክትሪክ ቅንብር ፕሮግራም
## (COMMUNITY ELECTRICITY AGGREGATION PROGRAM)
## የማስታወቅያ ደብዳቤ

ህዳር (November) 21 ቀን 2022

የተከበራችሁ የካምብሪጅ ነዋሪዎች ወይም የንግድ ስራ ባለቤቶች፡

ይህ ደብዳቤ የኤሌክትሪክ ክፍያዎን በተመለከተ አስፈላጊ መረጃ የያዘ ነው።

በአሁኑ ወቅት ፡ ኤቨርሶርስ ቤዚክ አገልግሎት (Eversource Basic Service) በሚባል የሙብራት/የኤሌክትሪክ አገልግሎት ነው በመገልገል ላይ የሚገኙት። ይህም ማለት የሙብራት/ኤሌክትሪክ አገልግሎት የሚያገኙት ኤቨርሶርስ((Eversource) ከሚባለው የኤሌክትሪክ ተቋም ነው። ይሄው ተቋም መብራት እንዲደርሶት ያደርጋል። አሱም ነው መብራት ወይም ኤሌትሪክ ከሌሎች የሚገዛሎት ማለት ነው።

ይሁንና፤ የካምብሪጅ ከተማ፤ **የካምብሪጅ ማህበረሰብ የኤሌክትሪክ ፕሮግራም** (Cambridge Community Electricity Program) የሚባል የኤሌክቲሪክ ፕሮግራም አለው። በዚህ ፕሮግራም ኤቨርሶርስ (Eversource) ኤሌክትሪክ ያቀርብሎታል፣ ከተማው ግን የራሱን የኤሌክትሪክ አቅራቢ ይመርጣል። ከተማው ይህንን ፕሮግራም ከጸሃይ የሚመነጭ አዲስ የኤሌክትሪክ ሃይል በካምብሪጅ ለመፍጠር ይጠቀምበታል። የእርሶ በዚህ ፕሮግራም ውስጥ መሳተፍ፤ አዲስ የኤሌክትሪክ ሃይል እንዲጨመር ያግዛሉ ማለት ነው።

**ይህንን ደብዳቤ ካገኙ በኋላ ምንም መልስ ካልሰጡ፤ በኦቶማቲክ መንገድ በካምብሪጅ የማህበረሰብ የኤሌክትሪክ ፕሮግራም (Cambridge Community Electricity Program) ውስጥ ይገባሉ።**

**በፕሮግራሙ ውስጥ በኦቶማቲክ መንገድ እንዳይገቡ፤ ከፕሮግራሙ መውጣት እንደሚፈልጉ የሚያስረዳው ደብዳቤዎ ወደ ፖስታ ቤት የገባው ከ ታህሳስ (December) 27 ቀን 2022 በፊት መሆኑን የሚያመለክት መሆን አለበት።**

**መሳተፍ ማለት፡** ኤቨርሶርስ (Eversource) የኤሌክትሪክ አቅራቢዎ መሆኑን ይቀጥላል። አሁንም የኤሌክትሪክ ሂሳቦን ከኤቨርሶርስ (Eversource) ማግኘቶን ይቀጥላሉ። መብራት ሲቋረጥቦትም የሚደውሉት እነርሱ ጋ ነው። ግን በዚሁ በሚደርስ የክፍያ ወረቀት (electric bill)፤ አቅራቢ (Supply) በሚለው ላይ ዳይሬክት ኤነርጂ (Direct Energy) የሚል ስም ተጽፎ ያያሉ። ለአቅራቢ (Supply) ምን ያህል ክፍያ እንደሚከፍሉ ሂሳቡን የሚያወጣው ደግሞ የካምብሪጅ ማህበረሰብ የኤሌክትሪክ ፕሮግራም (Cambridge Community Electricity Program) ነው።

**አነስተኛ ገቢ ላላቸው ሰዎች የሚደረግ የአቅርቦት መጠንና የነዳጅ እገዛ ለማግኘት ብቁ ሆነው ተገኝተው ከነበሩ፡ እነኝያኑ ጠቀሜታዎችን ማግኘትዎን ይቀጥላሉ። በዛው ሲደረግሎት በቆየው የእገዛ መጠን ይቀጥላል።**

**ላለመሳተፍ መምረጥ፡** ኤቨርሶርስ(Eversource) የኤሌክትሪክ አቅራቢዎ መሆኑን ይቀጥላል። በክፍያ ሂሳቦ ላይ ያለው የአቅራቢ ክፍያ በኤቨርሶርስ (Eversource) መሰረታዊ የዋጋ አገልግሎት (Eversource's Basic Service) መሰረት መታሰቡን ይቀጥላል።

### የመሳተፍ ጠቀሜታ

**መታደስ የሚችል የአካባቢ ኤሌክትሪክ (renewable electricity)** - ኤሌክትሪኮ፤ ከጸሃይ ከሚመነጭ ከከተማው አዲስ የኤሌክትሪክ ሃይል ፕሮጀክት መታደስ የሚችል ኤሌክትሪክ (renewable electricity) የ ሚጨምር ይሆናል። ውጤቱም ኤሌክትሪኮ ከተማው ከሚጠይቀው በላይ መታደስ የሚችል የኤሌክትሪክ ሃይል (renewable electricity) ይኖረዋል።

**አማራጮች** - ፕሮግራሙ ሁለት አማራጮችን ይሰጦታል: 1) ስታንዳርድ ግሪን (Standard Green)፤ በካምብሪጅ ውስጥ ካለው ከጸሃይ የሚመነጭ የኤሌክትሪክ ፕሮጀክት የሚገኘውን መታደስ የሚችል የኤሌክትሪክን ሃይል የሚጨምር እና 2) 100% ግሪን ፕላስ (Green Plus) 2) 100% መታደስ የሚችል ኤሌክትሪክ (renewable electricity) እና በካምብሪጅ ውስጥ ያለውና ከጸሃይ ከሚገኘው መታደስ ከሚችል ኤሌክትሪክ ፕሮጀክት። ስታንዳርድ ግሪን (Standard Green)ን በኦቶማቲክ መንገድ ልትመርጡ ይችላሉ ወይም 100% ግሪን ፕላስ (Green Plus) መመረጥ ይችላሉ(የዚሁ ጉዳይ ዝርዝር መረጃ ከወደኋላ ይገኛል)።

**ሊሆን የሚችል የገንዘብ ቁጠባ (Potential savings)** - የዚህ ፕሮግራም የክፍያ መጠን ኤቨርሶርስ (Eversource) በመደበኛ የክፍያ አገልግሎቱ ከሚያስከፍለው ዝቅ ያለ ሊሆን ይችላል። ይሁንና የኤቨርሶርስ (Eversource) መደበኛ የክፍያ አገልግሎት፤ በየስድስት ወሩ ለመኖርያ ቤቶችና አነስተኛ የንግድ ቤቶች፤ በየሶስት ወሩ ደግሞ ለትላልቅ የንግድ ቤቶች ደንበኞቹ የዋጋ ለውጥ (prices change) ያደርጋል። በመሆኑም፤ የፕሮግራሙ አከፋፈል ሁሌም ኤቨርሶርስ (Eversource) ከሚያስከፍለው በታች ይሆናል ለማለት አይቻልም፤ የገንዘብ ቁጠባ ይኖራል የሚል ዋስትናም ሊሰጥ አይቻልም።

## የካምብሪጅ ማህበረሰብ የ ኤሌክትሪክ ፕሮግራም

(Cambridge Community Electricity Program)

አዲሱ የመብራት አገልግሎት ክፍያ

**10.20 ¢/kWh**

የኤቨርሶርስ (Eversource) የመኖርያ ቤቶች መሰረታዊ አገልግሎት

**17.871 ¢/kWh**

ንግድ ቤቶችን በሚመለከት የኤቨርሶርስ (Eversource) ዋጋ ከበስተጀርባ ይገኛል ▶

## የደንበኛ እገዛ:

**1-844-379-9934**

## መሳተፍ አይፈልጉም?

**መሳተፍ ካልፈለጉ፡ ግዴታ የለቦትም ፤ ከፕሮግራሙ ለመውጣት የሚከፍሉት መቀጮ ወይም ገንዘብ የለም፡ ባፈለጉበት ግዜ ከፕሮግራሙ ሊወጡ ይችላሉ።**

ላለመሳተፍ ከመረጡ፡ በኤቨርሶርስ(Eversource) መሰረታዊ አገልግሎት ደንበኛ ሆነው ይቀጥላሉ።

ወደ ፕሮግራሙ ከመግባትዎ በፊት ለመውጣት ከፈለጉ፤ ከ **ታህሳስ (December) 27 ቀን 2022** በፊት ከሚከተሉት ውስጥ አንዱን ያድርጉ :

- ▶ ተያይዞ የተላከውን ካርድ ይፈርሙና ፖስታ ቤት የገባው ከ **ታህሳስ (December) 27 ቀን 2022** በፊት መሆኑን የሚያሳይ ምልክት ባለበት ፖስታ በመላክ፣ ወደ ደንበኞች አገልግሎት ክፍል በስልክ ቁጥር **1-844-379-9934** በመደወል ወይም ኦንላይን ወደ **masspowerchoice.com/cambridge** በመግባት ለመውጣት ይችላሉ።

ወደፊት ለመውጣት ከፈለጉ ከሚከተለው ውስጥ አንዱን ያድርጉ፡

- ▶ ወደ ደንበኞች መስመር በስልክ ቁጥር **1-844-379-9934** በመደውል ወይም በኦንላይን **masspowerchoice.com/cambridge** በመግባት ሊወጡ ይችላሉ፤

## የፕሮግራሙ አማራጮችና ዋጋዎች

| | | |
|---|---|---|
| **1. ምንም ካላደረጉ፡ በስታንዳርድ ግሪን (STANDARD GREEN) ይገባሉ፤** | | **10.20 ¢/kWh*** ለመኖርያ ቤቶች፣ ትልላቅና ትናንሽ ንግድ ቤቶች<br>(ይህም ከሁሉም ርካሽ የሆነ አማራጭ ነው) |
| **የሚታደስ የኤሌክትሪክ ሃይል ይዘት** | **የማሳቹሴትስን አነስተኛውን የሚታደስ የሃይል (renewable energy) ጥያቄን የሚያሟላ ነው እንዲሁም ከካምብሪጅ ከጸሃይ ከሚመነጭ የሚታደስ ሃይል ፕሮጀክት ተጨማሪ ሃይል ይጨምራል።**** | |
| **የዋጋ ግዜ (Price period)** | ምዝገባ- ጥር 2024 ሜትር ይነበባል | |
| **የሚያልቅበት ግዜ** | በማንኛውም ግዜ መውጣት ይችላሉ፡ የመውጣት ክፍያ የለም | |
| **2. መቶ በመቶ (100%) የሚታደስ ኤነርጂ (renewable energy) ከፈለጉ 100% አረንጓዴ ፕላስ (GREEN *PLUS*) ይምረጡ።**<br>▶ **100% አረንጓዴ ፕላስ (GREEN *PLUS*) ለመምረጥ ወደ ደንበኞች እርዳታ ክፍል በስልክ ቁጥር 1-844-379-9934 ይደውሉ።** | | **13.669 ¢/kWh*** ለመኖርያ ቤቶች፣ ትልላቅና ትናንሽ ንግድ ቤቶች<br>(ይህም ከሁሉም ርካሽ የሆነ አማራጭ ነው) |
| **የሚታደስ የኤሌክትሪክ ሃይል ይዘት** | **ከ ኑ ኢንግላንድ (New England) 100% ከሚታደስ የንጹህ ሃይል ፕሮጀክት እና ከካምብሪጅ ከጸሃይ ከሚመነጭ የሚታደስ ሃይል ፕሮጀክት ተጨማሪ ሃይል ይጨምራል።**** | |
| **የዋጋ ግዜ (Price period)** | ምዝገባ - ጥር ወር 2024 መለኪያ የተነበበት ወቅት | |
| **የሚያልቅበት ግዜ** | ባፈለጉበት ግዜ መውጣት ይችላሉ፡ ለመውጣት የሚከፍሉት ገንዘብ የለም። | |
| **3. ለመካፈል ካልፈለጉ በኤቨርሶርስ መሰረታዊ አገልግሎት (EVERSOURCE BASIC SERVICE) ውስጥ ይቆያሉ።** | | **17.871 ¢/kWh** መኖርያ ቤቶች<br>**17.827 ¢/kWh** አነስተኛ የንግድ ቤቶች<br>**30.613 ¢/kWh** ትላልቅ የንግድ ቦታዎች |
| **የሚታደስ የኤሌክትሪክ ሃይል ይዘት** | ይህ የሚታደስ የኤሌክትሪክ/መብራት ሃይል ጥያቄን የማሳቹሴትስ ክፍለሃገር የሚጠይቀውን አንስተኛውን ዋጋ ያሙዋላል። | |
| **የዋጋ ግዜ (Price period)** | ከሓምሌ (July) 1 ቀን 2022 እስከ ታህሳስ (December) 31 ቀን 2022 ለመኖርያ ቤቶችና ለትናንሽ ንግድ ቤቶች፤ ጥቅምት (October) 1 ቀን 2022 እስከ ታህሳስ (December) 31 ቀን 2022 ደግሞ ለትላልቅ የንግድ ቤቶች ክፍያ ይደረጋል። የኤቨርሶርስ (Eversource) የተመደበ የአገልግሎት ዋጋ ለመኖርያ ቤቶችና ለትናንሽ ንግዶች በየስድስት ወሩ፤ ለትላልቅ ንግድ ቤቶች ደግሞ በየሶስት ወሩ የዋጋ ለውጥ ይደረጋል። | |
| **የሚያልቅበት ግዜ** | በማንኛውም ግዜ ፕሮግራሙን ለቀው ለመውጣት ይችላሉ። የሚከፈል የመውጣት ክፍያ የለም። ይሁንና በተወሰነ የአከፋፈል ምደባ (fixed-price) አገልግሎት ስር የሚገኙ የ ሲ & አይ (የጂ-3 (G-3)፣ የቲ-2 (T-2) እና የደብሊው-አር (WR) ክፍያዎችና የመንገድ መብራት ደንበኞች፤ የክፍያ መስተካከል፤ የክሬዲት ወይም የክፍያ ወረቀት ሊደርሳቸው ይችላል። | |

* የስታንዳርድ ግሪን (Standard Green) ዋጋ እና 100% የግሪን ፕላስ (Green Plus) ዋጋ ሁለቱም ለአንድ ኪሎዋት (kWh) $0.00075 ያስከፍላሉ። የአስተዳደር ክፍያ እና ለአንድ ኪሎዋት (kWh) የ $0.002 የስራ ማካሄጃ ክፍያ አላቸው። የኤሌክትሪክ ማቀበል ስምምነት በሚደረግበት ግዜ የተደረሰ ደግሞ የፕሮግራሙ ዋጋዎች፤ በህጉ ላይ ቀጥታዊ የቁሳቁስ ዋጋ ከፍ የማለት/ለውጥ ከተደረገ፤ ሊጨምሩ ይችላሉ።

** በስራ ማካሄጃ ተጨማሪ (operational adder) ምክንያት የተሰበሰበ ገንዘብ ሁሉ ከጸሃይ በሚገኝ የኤሌክትሪክ ሃይል እድገት ፕሮጀክት ጥቅም ላይ እንዲውል ይደረጋል። ከተማው፤ በዚህ ፕሮጀክት የመነጨው የአር-ኢ-ሲ-ኤስ (RECs) ሃይል ከፉሉ በስታንዳርድ ግሪን (Standard Green) እና በ100% ግሪን ፕላስ (Green Plus) ኤሊክትሪክ ሃይል ተሳታፊዎች ጥቅም ላይ እንዲውል ያደርጋል።

## በብዛት የሚጠየቁ ጥያቄዎች

**ቅናሽ የማግኘቱ ሁኔታ ዋስትና አለውን?** የለውም። የኤቨርሶርስ (Eversource) የተመደበ አገልግሎት ዋጋዎች፤ ባሎት የአገልግሎት አካውንት ወይም ሂሳብ በመመርኮዝ፤ የክፍያው መጠን በየስድስት ወሩ ወይም ከዛ ባነሰ ግዜ ውስጥ ይቀየራል። በመጪ ግዚያት የሚከፈሉ ክፍያዎች ምን ያህል እንደሚሆኑ አይታወቅም። ለመኖርያ ቤቶች፤ ለትናንሽና ትላልቅ ንግድ ቤቶች የኤቨርሶርስ (Eversource) የመደበኛ ክፍያ ዋጋዎች በሚቀጥለው ጥር (January) 1 ቀን 2023 ላይ ይቀየራሉ። በአሁኑ ወቅት ያለው የ ክፍያ መጠን ምን ያህል እንደሆነ ለማወቅ ወደ https://www.eversource.com ገብተው ይጎብኙ።

**ከአንድ የሃይል አቀባይ ተቋም ጋር ውል ተፈራሜአለሁ፤ ምን ማድረግ አለብኝ?** ከአንድ የኤሌክትሪክ ሃይል አቀባይ ጋር ውል ካሎትና ከዚሁ አቀባይ ጋር ባደርጉት ውል መቆየት ከፈለጉ፤ ከዚህ ከካምብሪጅ ማህበረሰብ የኤሌክትሪክ ፕሮግራም (Cambridge Community Electricity Program) መውጣት አለቦት። ከፕሮግራሙ ለመውጣት የሚወሰዱትን እርምጃዎች ካልወሰዱና ካልወጡ፤ በኡቶማቲክ መንገድ ይመዘገባሉ፤ ከዛም በላይ ከኤሌክትሪክ አቀባዮ ቅጣት ሊያስከትልቦት ይችላል።

**ከግብር ነጻ የሆነ አካውንት ነው ያለኝ፤ ይህንን ያለኝን ከግብር ነጻ የሆነ ሂሳቤን እንዴት ነው መጠበቅ የምችለው?** እንደ አንድ የፕሮግራሙ የኤሌክትሪክ አቅርቦት የክፍያ አካል መጠን፤ የሚከፍሉት ግብር ይመደብሎታል። ከግብር መክፈል ነጻ የሆኑ ደንበኞች፤ ተገቢ የሆኑ ከግብር ነጻ መሆንዎን የሚያመለክቱ ዶኩመንቶችን መለየትና ወደ ዳይሬክት ኤነርጂ (Direct Energy) ማቅረብ የእነሱ ሃላፊነት ነው። ዶኩመንቶችዎን የት እንደሚያቀርቡ መረጃ ለማግኘት ወደ masspowerchoice.com/cambridge ገብተው ይጎብኙ።

ተጨማሪ ጥያቄዎች ካልዎት፣ እባክዎን ከደንበኞች እገዛ ክፍል አባሎች (customer support) ጋር በ **1-844-379-9934** ደውለው ይገናኙ ወይም ወደ **cambridge@masspowerchoice.com** ይጻፉ፣ ወይም በኢንተርኔት ወደ **www.masspowerchoice.com/cambridge** ይግቡ። የፕሮግራማችን አማካሪዎች እርስዎን ለመርዳት ደስተኞች ይሆናሉ፡፡ ወይም ደግሞ የካምብሪጅ ከተማን በቀጥታ በ 617-349-5323 ማግኘት ይችላሉ።

ይ-አን ሁዋንግ (Yi-An Huang)
የከተማ አስተዳዳሪ (City Manager)

# የመውጫ መመለሻ ካርድ

## የካምብሪጅ ማህበረሰብ ኤሌክትሪክ ፕሮግራም

X ____________________________________________

ፊርማ ቀን

## የመውጫ መመርያዎች

በካምብሪጅ ማህበረሰብ የኤሌክትሪክ ፕሮግራም ውስጥ ለመሳተፍ ከፈለጉ ምንም አይነት እርምጃዎችን መውሰድ አይኖርቦትም።

**በፕሮግራሙ ለመሳተፍ ካልፈለጉ፤ መውጣት አለቦት።** የሚወጡት መንገድ ፖስታ በመላክ ከሆነ፡

1. **በዚህ ካርድ ላይ ቀኑን ጽፈው ይፈርሙ**
2. **ካርዱን በተካተተው ፖስታ ውስጥ ያሽጉ**
3. **ፖስታውን በፖስታ ቤት በኩል ይላኩ**

ይህ ካርድ ስሙ ከወደላይ ተጽፎ በሚገኘው የመዝገብ ቤት ሹም መፈረም አለበት። ኦቶማቲክ ምዝገባን ለማስወገድ፤ ካርዱን የያዘው ፖስታ ደግሞ ፖስታ ቤት የገባው ከ **ታሕሳስ (December) 27 ቀን 2022** በፊት መሆኑን የሚያመለክት ምልክት ሊኖረው ይገባል።፡ከፕሮግራሙ በማንኛውም ግዜ ለመውጣት ከፈለጉ ወደ masspowerchoice.com/cambridge በመግባት ወይም ወደ ደንበኞች አገልግሎት ክፍል በስልክ ቁጥር 1-844-379-9934 በመደወል ሊወጡ ይችላሉ።